# የክፍል 8 ቫውቸሮች

# ተከራዮች: መብቶችዎን ይወቁ!

**ምንም እንኳን ኪራይ ቢኖርቦት፣ የቫውቸር ካርድዎ ቢጠፋ ወይም ውሎትን ቢጥሱ አከራዮት የማይችለው፡**

- እንዲለቁ የበር ቁልፎችን መቀየር
- አገልግሎቶችዎን ማቋረጥ (መብራት፣ ውሃ፣ጋዝ )
- የመንግሥት ተወካይ ሳይመጣ እቃዎትን መንገድ ላይ አውጥቶ መጣል

**ይህ ከደረሰብዎት የማስለቀቂያ ባለመብቶች ጋር ደውለው ይማከሩ።**

## የክፍል 8 ቫውቸር ምንድን ነው?

- የክፍል 8 ቫውቸር በቤቱ ፈንታ ከአንድ ሰው (**የቫውቸሩ ባለቤት**) ጋር የተያያዘ **"የመኖሪያ ቤት ድጎማ"** ነው። ቤቱን የሚለቁ ከሆነ **የቫውቸር ካርድዎን ከእርስዎ ጋር መውሰድ** ይችላሉ።
- የቫውቸር ካርድ ካልዎት፣ **ከወርሃዊ ገቢዎ 30%** ያህሉን ለቤት ኪራይ ይከፍላሉ። መንግሥት ልዩነቱን አሟልቶ የቀረውን የቤት ኪራይ ለባለንብረቱ በየወሩ የሚከፍል ይሆናል።
- አንዳንድ ጊዜ ሕንፃዎች **"በፕሮጀክት ላይ የተመሰረተ ክፍል 8"** የሚባል ነገር ይኖራቸዋል። ይህ ከአንድ ሰው ይልቅ ከህንፃው ጋር የተያያዘ የተለየ የመኖሪያ ቤት ድጎማ ሥርዓት ነው። በፕሮጀክት ላይ የተመሰረተ ክፍል 8 ሥርዓት ካለው ቤት **ከለቀቁ**፣ ድጎማው **ከእርስዎ ጋር አይመጣም**።
- እያንዳንዱ የክፍል 8 ቫውቸር ባለቤት የራሱ **ጉዳይ አስፈጻሚ** ይኖረዋል። የእርስዎን ማወቅዎን ያረጋግጡ!

## በክፍል 8 ቫውቸር ውስጥ ግዴታዎቼ ምንድን ናቸው?

- **በ60 ቀናት ውስጥ መኖሪያዎትን ፈልገው ያግኙ።** አከራዮች ክፍል 8ን መቀበል አይጠበቅባቸውም። ለተጨማሪ ጊዜ የቫውቸሩ ጊዜ ከመጠናቀቁ **በፊት** ማራዘሚያ መጠየቅዎን ያረጋግጡ!
- **በየዓመቱ እና የቤተሰብዎ መጠን ወይም ገቢዎ በሚቀየርበት ጊዜ በድጋሚ ያረጋግጡ።** የቤተሰብዎን የገቢ መጠን ማረጋገጫ ለክፍል 8 ጉዳይ አስፈጻሚዎ ይስጡ።
- **ከኪራይ ዋጋ የእርስዎን ድርሻ በየወሩ ይክፈሉ።** ገቢዎ ከተለወጠ ለጉዳይ አስፈጻሚዎ ይንገሩ። በኪራይዎ ላይ ተጽእኖ ሊያሳድር ይችላል! አስፈላጊውን ስምምነት እና የማረጋገጫ ቅጾችን **ይፈርሙ**።
- የኪራይ ውልዎን **አይጣሱ**፣ ቦታውን ጤናማ ያልሆነ ወይም አስጊ አያድርጉ፣ ወይም አደገኛ እና የሚያስፈራ ነገር አያድርጉ። **ይህ የእርስዎን እንግዶችም ያካትታል።**
- የሚፈልጉት ጥገና ካለ **ለአከራይዎ እና ለጉዳይ አስፈጻሚዎ በጽሁፍ ያሳውቁ።**

SECTION 8

LEGAL AID SOCIETY OF MIDDLE TENNESSEE AND THE CUMBERLANDS (833) 837-የቤት

AMAC American Muslim Advisory Council (615) 988-6460

conexión américas (615) 701-7957

Nashville Hispanic Bar Association

**ይህ መረጃ ለዴቪድሰን ክልል ብቻ ነው።** እዚህ የቀረበው መረጃ የህግ ምክርን አይመሰርትም፤ ለመመስረት የታሰበም አይደለም። የሕግ ችግር ካጋጠመዎት፣ እባክዎን ለግል ጠበቃዎት ይደውሉ ወይም በአካባቢዎ የሚገኘውን የመካከለኛው ቴነሲ የሕግ ድጋፍ ማህበር እና የኩምበርላንድ ቢሮ በ1-800-238-1443 ወይም የናሽቪል የሂስፓኒክ ባር ማህበርን በ1-615-701-7957 ይደውሉ።

በ5/23 ተሻሽሏል።

# የክፍል 8 ቫውቸሮች

# ተከራዮች: መብቶችዎን ይወቁ!

## ክፍል 8 የቫውቸር ካርዴን **ለማቋረጥ** የሚሞክረው መቼ ነው?



## ቫውቸሬ **የሚቋረጥ** ከሆነ ምን ይፈጠራል?

የሚያገኙትን እርዳታ ከማቋረጣቸው በፊት በክፍል 8 ችሎት ቀጠሮ የማግኘት መብት አልዎት። ቫውቸርዎ እየተቋረጠ ነው የሚለው ወረቀት ላይ ካለው ቀን ጀምሮ በ10 **ቀናት** ውስጥ የ**“ቅሬታ” ስብሰባ** እንዲደረግ ይጠይቁ።

- ለችግሩ ማንኛውንም ዓይነት **ማረጋገጫ** ወይም **መረጃ** ከእርስዎ ጋር ወደ ቅሬታ ሰሚ ስብሰባዎ ይዘው ይምጡ።
- የመጀመሪያው ስብሰባዎ በአብዛኛው **መደበኛ ያልሆነ** ስብሰባ ይሆናል። ችግሩን በዚያ መፍታት ካልቻሉ፣ ብዙ ጊዜ **መደበኛ** ችሎት መጠየቅ ይችላሉ።
- ክፍል 8ን በክርክር ከተሸነፉ 100% ለኪራይ ክፍያው ኃላፊነት ይወስዳሉ። ኪራዩን መክፈል ካልቻሉ፣ አከራዩ እርስዎን **ለማስወጣት** ሊሞክር ይችላል።
- የኪራይ ክፍያዎ የዘገየ ቢሆንም እንኳን አከራይዎ የበር ቁልፎችን ሊለውጥ ወይም ሊያባርርዎት **አይችልም**። መጀመሪያ **ፍርድ ቤት** ሊያቀርብዎት ይገባል።

**የፍርድ ቤት መጥሪያ ከደረስዎት ወደ ፍርድ ቤት ይሂዱ! ካልሆነ በቀላሉ ይሸነፋሉ።**

## ቫውቸሬን ሳላጣ መውጣት የምችለው እስከመቼ ድረስ ነው?

የኪራይ ውልዎ ካለቀ በኋላ ለአከራይዎ እና ለክፍል 8 ጉዳይ አስፈጻሚዎ **የጽሁፍ ማሳሰቢያ** ከሰጡ የ**ቫውቸር** ካርድዎን ይዘው መንቀሳቀስ ይችላሉ።



ለአከራይዎ እና ለጉዳይ አስፈጻሚዎ ስለሚያስፈልጉ ጥገናዎች በጽሁፍ ከነገሩና ባለንብረቱ ግን አሁንም ካላስተካከላቸው ክፍል 8 ሊጠቅሳቸው ይገባል። ከዚያ በኋላ ባለንብረቱ አሁንም ነገሮችን ካላስተካከለ፣ በቫውቸርዎ መንቀሳቀስ መቻል አለብዎት።

**SECTION 8**

LEGAL AID SOCIETY of Middle Tennessee and the Cumberlands (833) 837-የቤት

AMAC American Muslim Advisory Council (615) 988-6460

conexión américas (615) 701-7957

Nashville Hispanic Bar Association

**ይህ መረጃ ለዴቪድሰን ክልል ብቻ ነው።** እዚህ የቀረበው መረጃ የህግ ምክርን አይመሰርትም፤ ለመመስረት የታሰበም አይደለም። የሕግ ችግር ካጋጠመዎት፣ እባክዎን ለግል ጠበቃዎት ይደውሉ ወይም በአካባቢዎ የሚገኘውን የመካከለኛው ቴነሲ የሕግ ድጋፍ ማህበር እና የኩምበርላንድ ቢሮ በ1-800-238-1443 ወይም የናሽቪል የሂስፓኒክ ባር ማህበርን በ1-615-701-7957 ይደውሉ። በ5/23 ተሻሽሏል።